DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

ውድ ወዳጆች፤

ዛሬ፣ የዲሲፒኤስ የህዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS)፣ ቻንስለር የሆንኩበት የመጀመሪያው ቀን ሆኖ የሚያዝ ሲሆን፣ እዚህ በመሆኔ እጅግ አስደስቶኛል፣ ክብርም ተሰምቶኛል! በእድገቴ በርካታ የመጀመሪያ ቀናትን አይቻለሁ። ከትምህርት ቤት ከመመረቄም በፊት 10 ትምህርት ቤቶች ገብቼ የተማርኩ ሲሆን እስከ ዛሬም ድረስ የተስፋ ስሜት እና ከአዲስ ጅማሬም ጋር አብረው የሚመጡትን ተስፋዎች ይዣቼው እጓዛለሁ።

ዛሬ ዲሲፒአስን (DCPS) የምመራበት የመጀመሪያው ቀኔ ሲሆን ግሩም ለሆኑ ተማሪዎች፣ ዲሲፒኤስን ከመላ ሀገሪቱ፣ በጣም ፈጣን መሻሻል የሚታይበት እና ብዙውን ጊዜም የሚመለከቱት የትምህርት ዲስትሪክት እንዲሆን ለሚያደርጉ ግሩም ለሆኑ ተማረዎች፣ መምህራን እና ሠራተኞች፣ ለወላጆች እንደማንኛውም ቀን ልዩ ቀን ሆኖ የሚታሰብ ነው። ለእያንዳንዱ ወጣቶቻችን የሚገባቸውን በዓለም፣ ደረጃውን የጠበቀ ትምህርት ለመስጠት እንድንችል የት የት ላይ እጅግ በበለጠ ጠንክረን መሥራት እንደሚገባን ከእናንተ ለመማር፣ የዲሲፒኤስን ማኅበረሰብ ለማወቅ እየጓጓሁ ነው።

ሙያየ በትምህርት አማካይነት ተመጣጣኝነትን (equity) በማሻሻል ዙሪያ ላይ የተገነባ ነው። ለአለፉት ሦስት ዐማታት የኦክላንድን የተቀናጀ የትምህርት ዲስትሪክት (Oakland Unified School District) እመራ የነበርኩ ሲሆን፣ ከዚህ በፊት ቀደም ብሎ የዴንቨር የሕዝብ ትምህርት ቤቶችን (Denver Public Schools) በትምህርት ቤቶች ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅነት፣ ርእሠ መምህርነትና መምህርነት አገልግያለሁ። የእግር ኳስ ጨዋታ እና የመስክ የስፖርት ውድድርን በአሠልጣኝነት፣ እና የንግግር እና የክርክር ክበቦችን የበላይ ጠባቂ በመሆን አገልግያለሁ።

እርግጠኛውን፣ ትምህርት ቤትን እወዳለሁ። ወጣቶች ሲማሩ እና ችሎቶቻቸውን ሲገነዘቡ እና ሲረዱ ማየት እወዳለሁ። በዲሲፒኤስ የሚማር እያንዳንዱ ተማሪ፣ ትምህርት ቤትን እንዲወዱ እፈልጋለሁ። ያፈራኋቸው የትምህርት ውጤት እድገቶቼ ጠንክሮ የመሥራት እና እና የተፈታተኑኝና በእኔም ላይ እምነት የጣሉብኝ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች መምህራን ብርቱ የሥራቸው ውጤት ፍሬ ነው። በትምህርት እድሎች አማካይነት ምን መቀዳጀት እንደሚቻል የማውቅ እና ትምህርት ቤቶች፣ ተማሪዎች፣ ወላጆች፣ እና ማኅበረሰበቦች በመልካም የሚስተናግዱባቸው እና ዕሴቶቻቸው የሚንፀባረቁባቸው ተቋማት ሆነው እንዲገኙ እርግጠኛ ለማድረግ እፈልጋለሁ።

በተከታታዮቹ ጥቂት ወራት፣ የትምህርት ቅጥር ግቢዎችን በመጎብኘት፣ ከመምህራን እና ከወላጆች ጋር በመገናኘት፣ የትምህርት ተግባር የሚመለከታቸው አካላት የሚሉትን በማዳመጥ ስለ ትምህርት ቤቶች ያላችሁን ራዕይ ለማወቅ እፈልጋለሁ። ለእኔ ዛሬ ከምገኝበት ሁኔታ የበለጠ፣ ነገ ትንሽ ዕውቀት ጨምሬ ብልህ ሆኔ መገኘት አስፈላጊ ጉዳይ ሲሆን፣ ይህንንም በቀላሉ ለመግለጽ በእንደዚህ ዐይነት ሁኔታዎች ላይ በመሰታፍ የምቀስማቸው መረጃዎች በመሪነቴ የማደርጋቸው ውሳኔዎች ብልህነት ያላቸው እንዲሆኑ ይረዱኛል ብየ አምናለሁ። ሀሳቦቻችሁን በምን ዐይነት ሁኔታ ማካፈል ስለምትችሉባቸው መንገዶች የበለጠ መረጃ በቅርቡ እንዲደርሳችሁ እናደርጋለን።

በዲሲፒኤስ (DCPS) ደጋግመን የምናሰማው ቃላችን (mantra) ይህንን እንፈጽመዋለን የሚል ሲሆን፣ ነገር ግን ለብቻችን ተግባራዊ ማድረግ እንደማንችል እንገነዘባለን። ይህ ከምን ጊዜውም የበለጠ አሁን የምናየው ሀቅ ነው። የዲሲፒኤስ ማኅበረሰ (DCPS) አካል የሆናችሁ ሁሉ፣ ተስፋችሁን የማስተጋባት፣ ስለሚያሳስቧችሁ ጉዳዮች በሀቀኝነት መቆም እና ለስኬቶቻችን ዋጋ በመስጥት ለማክበር ጽኑ እምነቴ በእናንተ ላይ ነው። ከሁሉም በላይ ይህ ተግባር የተሳካ ኣንዲሆን ለማድረግ ከእናንተ ጋር ለመጎዳኘት በጉጉት እጠባበቃለሁ።

ከአክብሮት ጋር፣

Antwan Wilson
ቻንስለር፣ ዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Chancellor, DC Public Schools)